# ይቺ ጠጋ ጠጋ …

አፍኤጋ ሶቾአ  ከአዳማ

አንዳንድ የተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሕገወጥነት ክፉኛ ተጠናውቷቸው ከአግባብ ውጭ የሆኑ አካሄዶችን የሙጥኝ ብለው ይስተዋላሉ፡፡ ከሕገወጥ አካሄድ ጋር የተቆራኙ ፓርቲዎች ከወንጀል ጋር ከተፋቱ ህልውናቸው የሚያከትምለት ስለሚመስላቸው ከቀይ መስመር ርቀው መታየትን አይፈልጉም፡፡ ሰሞኑን የአንድነት ፓርቲ ቅጥያ ሆኖ የበቀለው የእነ ፕሮፌሰር መስፍን ፓርቲ ወይዘሪት ብርቱካን ሚደቅሳን የፓርቲው ተቀዳሚ ሊቀመንበር አድርጎ መርጧታል፡፡ ለመሆኑ ወይዘሪት ብርቱካን ማን ናት? የት ነች? የእነ ፕሮፈሰር አንድነት ብርቱኳንን በሊቀመንበርነት ለመምረጥ ለምን ፈለገ? እኔ የህግ በለሙያ እንጂ ፖለቲከኛ አይደለሁም፡፡ የእነዚህ ሰዎች አካሄድ አንድ ነገር  ስለጫረብኝ  ይህችን ልጽፍ ወደድኩ፡፡

ወይዘሪት ብርቱካን ጥሩ የህግ ባለሙያ፣ ለአጭር ጊዜም ቢሆን በሙያቸው ሃገራቸውን ያገለገሉና 1997 የቀድሞው ቅንጅት ወህደት ሲያደርግ ግለሰቧ የፓርቲው ተቀዳሚ ምክትል ሊቀመንበር የነበሩ ናቸው፡፡ ከምርጫ 97 በኋላ የቀድሞው ቅንጅት አመራሮች በፈፀሙት ስህተት ለበርካታ ወገኖቻችን ህይወት መጥፋትና ንብረት መውደም ምክንያት ሆነው በህግ አግባብ ወደ ማረሚያ ቤት ወረዱ፡፡ ፍርድ ቤትም ሂደቱን ተመልክቶ ጥፋተኛ ሆነው በመገኘታቸው የእድሜ ልክ እስራት መወሰኑ የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው፡፡

እንግዲህ በዚህ አግባብ ወደ ቃሊቲ የወረዱት የቀድሞው የቅንጅት አመራሮች ህዝብንና መንግሥትን ይቅርታ ጠይቀው በቅድመ ሁኔታ ላይ የተመሠረተ ይቅርታ ተሰጥቷቸው ከእሥር እንዲፈቱ ተደረገ፡፡ እነዚህ ግለሰቦች ከእስር ሲፈቱ ህገ መንግሥቱንና ህገ መንግስታዊውን ስርዓት ማክበር ብቻ ሳይሆን ማስከበርም እንዳለባቸው ከስምምነት ተደርሶ ማንኛውም ማኅበራዊም ሆነ ፖለቲካዊ ጥቅሞቻቸው ሳይጓደሉባቸው ከህብረተሰቡን እንዲቀላቀሉ ተደረገ፡፡

ይቅርታ ከተቸራቸው መካከል አንዷ ወይዘሪት ብርቱካን ናቸው፡፡ ግለሰቧ በአደባባይ ይቅርታ ጠይቀው ከተፈቀደላቸው ቡኋላ መልሰው በአደባባይ ይቅርታ አልጠየኩም ስላሉ የህግ የበላይነት ለማስከበር ወደ ማረሚያ እንዲገቡ ተደረገ።

የወይዘሪት ብርቱካን ምደቅሳ የይቅርታ መነሳት የህግ የባላይነትን ማስጠበቅ እንጂ የፖለቲካ እስረኛነት ጉዳይ እንዳልሆነ ይሰማኛል ፡፡ ምክንያቱም በወቅቱ የመገናኛ ብዙሀን እና የግል ጋዜጦች  እንደገለፁት ለይቅርታው መሰረዝ ምክንያት የሆነው ግለሰቧ በስዊዲን እና በጀርመን አገር በተደረገ ስብሰባ ላይ በመገኘት “ያቀረብኩት የይቅርታ ጥያቄ የለም ወይም አልጠየኩም:: ከእስር የተፈታነው በሽማግሌዎች ድርድር እና ሾላ በድፍን በሆነ መንገድ እንጂ ይቅርታ ስለጠየኩ አይደለም፡፡ እናም በህግ በተመሰረተ አግባብ የይቅርታ ጥያቄ አላቀረብኩም፡፡ የተሰጠኝም ይቅርታ የለም” ብለው መግለጫ በመስጠታቸው ነበር፡፡

በወቅቱ ብዙ ኢትዮጵያውያን የመንግሥትን አርቆ አሳቢነትንና የሃገር ሽማግሌዎችን የተሳካ ጥረት አድንቀን የሃገራችን የቆየ የሽምግልና ሂደት ዛሬም ውጤትማ ሆኖ ስናየው በባህላችን ኮራን።የቅንጅት አመራሮችም ቃል የገቡትን ይፈጽማሉ  የሚል እምነት አድሮብ ነበር።

ለቅንጅት አመራሮች ይቅርታ ሲሰጥ የነበሩ ሁኔታዎች ስንመለከት  በመጀመሪያ ይቅርታ ጠያቂዎቹ ለተፈፀመው ጥፋት ወይም ለንብረት መውደምና ለንፁኃን ዜጎች ህይወት ማለፍ  በግልና በጋራ ኃላፊነት እንደሚወስዱ፤ ሁለተኛ፣ ለወደፊትም በዚህ መሰል ተግባር እንደማይሳተፉ፤ ሶስተኛ፣ ህገ መንግስቱን የማክበርና የማስከበር ተግባር በአግባቡ እንደሚወጡ፤ አራተኛ፣  በህግ የተደራጁ የመንግስት ስልጣን አካላትን ተግባር ተቀብለውና አክብረው እንደሚንቀሳቀሱ ተስማምተው ነበር፡፡ በእነዚህ ነጥቦች ተስማምተው በፈርማቸው ይቅርታ ጠየቁ መንግስትም በቅድመ ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ይቅርታ ሰጣቸው  በእዚህ ሁናቴ ከማረሚያ ቤት የወት ግለሰብ እንዲህ ያለ የክህደት ድርጊት መፈጸማቸው አግባብ እንዳልሆነ  የህግ ባለሙያ ለሆኑት ወይዘሪት ብርቱካን  የሚጠፉቸው አይመስለኝም፡፡

ማንም በቀላሉ እንደሚረዳው ወይዘሪት ብርቱካን ሶስተኛ እና አራተኛውን ቅድመ ሁኔታዎችን ጥሰዋል:: ለምን ቢባል? የይቅርታ ቦርዱ ባቀረበው የውሳኔ ሀሳብ መሰረት በርዕሰ ብሔሩ የተሰጣቸውን ይቅርታ በመናድ ምንም ይቅርታ አልጠየኩም ይቅርታም አልተሰጠኝም በማለታቸው በህገመንግስቱ የተሰየመን አካል ተግባር ያለመቀበል እና የህገመንግስቱን አንቀጽ 9 (2) በሁሉም ዜጋ ላይ የተጣለውን የህገመንግስቱን የበላይነት አለመቀበልን እና አለማክበርን ያሳያል እላለሁ።

ወይዘሪት ብርቱካን ይቅርታ አልጠየኩም ብለው በይፋ ከተናገሩ ማንም አስገድዶ ይቅርታ ሊያስጠይቃቸውና ሊያሰጣቸው አይችልም፤ እናም የፍርድ ውሳኔው የፀናባቸው ዘንድ ወደ ማረሚያ ወረዱ፡፡ ማንም ለእራሱ ከእራሱ በላይ የሚያውቅ የለም እና ግለሰቧ የመረጡትን ፈፅመዋል፡፡ ለዚህም እስከ ዛሬ ድረስ ላደረጉት ድርጊት የተፀፀቱ አይመስለኝም፡፡

እኔ በራሴ አቋም ያለው ሰው ደስ ስለሚለኝ ከወይዘሪቷ ድርጊት ይልቅ በተቃዋሚ ፓርቲ ስም የተሰባሰቡት አመራሮች አካሄድ ግራ እያጋባኝ ነው፡፡ ምክንያቱም ግለሰቧ ይቅርታ አልጠየኩም ካሉ የፍርድ ቤትን ውሳኔን መቀበል ግዴታ ነው፡፡ ይህን በማራገብ የሚገኝ የፓለቲካ ትርፍ ጠቃሚ አይመስለኝም። የህግ የበላይነት ማለት ይህ ነው።

ይህንን ድርጊት መንግሥት እንደ ቀላል አይቶ ለምን አያልፍም ለሚሉት ግለሰቦች መንግሥት የህግ የበላይነት የማስጠበቅ ግዴታ ስላለበት የወይዘሪቷ ወደ ማረሚያ መመለስ ከዚህ አኳያ ሊታይ ይገባል። ምክንያቱም የህግ የበላይነትን ማስከበር ከድርድር የሚቀርብ መሆን የለበትም። የህግ የበላይነትን ካልተከበረ ማንም እንዳሻው ስለሚሆን ሁከት፣ ብጥብጥ እና ቀውስ ስለሚነግስ ወጥቶ መግባት፣ ወልዶ መሳም ስለማይቻል ድርጊቱ በህግ አግባብ መቋጨቱ አግባብ ይመስለኛል::

በይቅርታ አዋጁ አንቀጽ 12 (1) መሠረት የይቅርታ ጥያቄው በጠያቂው ወይም በወኪሉ ወዘተ መቅረብ አለበት ስለሚል ግለሰቧ ደግሞ በህግ አግባብ የጠየኩት ይቅርታ የለም ብለው ስለካዱ ይቅርታ ላልጠየቀ ሰው ይቅርታ ማድረግ (መስጠቱ ) አግባብ አይሆንም፡፡ ይቅርታው መሰረዙም ፖለቲካዊ ሳይሆን ህጋዊ አካሄድ

መሆኑን መረዳት ይቻላል:: ከፖለቲካ ተሳትፎ ለማጨናገፍም እንዳልሆነ መገመት ይገባል::

ወይዘሪት ብርቱካን  ጉዳዩ ፖሊስ ዘንድ ከደረሰ በኋላስ ለምን በተሰጣቸው እድል አልተጠቀሙም? ወይዘሪት ብርቱካን ፖሊስ ለምን ይጠራኛል? መግለጫዬን እንዳስተባብልስ ለምን ሶስት ቀን የጊዜ ገደብ ይሰጠኛል ወዘተ ያሉትን ስንመለከት ግለሰቧ ለፍትህ አካሉ መልካም አመለካከት ያላቸው አየመስለኝም። ፖሊስ ስልጣን የመነጨው ከህገ መንግስቱ አንቀጽ 9 (2) አንቀጽ 51 (6) የህዝብን ሰላም እና ደህንነት ለመጠበቅ ቀሚልና ከሌሎች ህግ እና ደንብ መሆኑን ወይዘሪት ብርቱካን ያጡታል ብዬ አላስብም:: ለአንዲት የሕግ ባለሙያ እንዲህ ያለው ድርጊት ምን እንደሚያመጣ ያጡት አይመስለኝም፣ ዛሬ እሳቸው ህግንና ህግ አስከባሪን ካላከበሩ ነገ ስልጣን ቢይዙ ማን ስርዓት ያስከብርላቸዋል?

እ.ኤ.አ. በዲሴምበር 1966 የፀደቀው ዓለም አቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ኮቬናንት (ስምምነት አዋጅ) በአንቀጽ 26 እንደሚገልፀው ሁሉም ሰው በህግ ፊት እኩል ነው:: በዘር፣ በቀለም፣ በፆታ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ ወዘተ... ልዩነት አይደረግበትም ይላል:: የሀገራችን ህገ መንግስትም በአንቀጽ 25 በተመሳሳይ ሁሉም ሰው በህግ ፊት እኩል መሆኑን ይደነግጋል:: ወይዘሪት ብርቱካን "የፓርቲ ሊቀመንበር "እና ሴት በመሆናቸው ከሌላው ዜጋ የተለየ ምንም መብት እንደሌላቸውና በህገ መንግስቱ የሰፈረው የድጋፍ እርምጃ መብትም (Affirmative measures) ቢሆን እንኳ ለዚህ ዓላማ እንደማያገለግል ግልፅ ሊሆን ይገባል:: ሴት ፖለቲከኛ ነኝና እንደፈለኩ ልሁን የሚል አስተሳሰብ ተቀባይነት አይኖረውም:: ወደፊትም እንዲህ ዓይነት ጉዳይ  በአገራችን ሰላምና መረጋጋት ለእድገትና ለዴሞክራሲ እድገት እንቅፋት በመሆኑ በሃገራችን እንዲህ ያለው አጉራዘለል ድርጊት እንዳይለመድ  “ሳይቃጠል በቅጠል”  ነውና መቀጨት ይኖርበታል፡፡ ስለዚህ መንግስት የህግ የበላይነትን ለማስከበር ትኩረት መስጠቱና እርምጃ መውሰዱ አግባብ ይመስለኛል::

ወይዘሪት ብርቱካን ቀና አስተሳሰብ ቢኖራቸው ኖሮ በፖሊስ ሦስት ቀን የጊዜ ገደብ ሲሰጣቸው ማስተባበል ይችሉ ነበር:: ሊቀመንበሯ በዚህ እድልም አለመጠቀማቸው

በጣም የሚያሳዝን ጉዳይ ነው:: ስለዚህ ዳግም በሳቸው ምክንያት ሀገርና ህዝብ የ1997ቱን ዓይነት ሁከትና ብጥብጥ ውስጥ መግባት ተገቢ ስላልሆነ እንዲህ ላለው ሁኔታ የህግ እርምታ መሰጠቱ ተገቢ ነው እላለሁ፡፡

ባጠቃላይ የወይዘሪት ብርቱካን የይቅርታ አሰጣጥና ይቅርታው የተነሳበት ምክንያት ማንም ገለልተኛ ሰው ሊፈርደው የሚችለው ነው። መንግስት ግልጽና ህገ መንግስቱን መሰረት ባደረገ ኃላፊነት በተሞላበት አኳኋን የወሰደው እርምጃ አግባብ ይመስለኛል። በተጨማሪም መንግስት ጉዳዩን አስመልክቶ በየወቅቱ ይወስዳቸው የነበሩትን እርምጃዎች ለህብረተሰቡ ይገልፅ ስለነበረ ሂደቱን ለመፈተሽ መንገዱን ቀላል ያደርገዋል፡፡ ወይዘሪት ብርቱካን ይቅርታ አልፈልግም በማለታቸው ወደ ማረሚያ ቤት ተመለሱ እንጂ ከሌሎች የቅንጅት አመራሮች የተለየ የፈፀሙት አንዳችም ነበር የለም፡፡

መንግስት በሃገሪቱ ውስጥ ህግ የማስከበር ኃላፊነት አለበት፡፡ የህግን የበላይነትን ማስከበር ያልቻለ መንግስት ሊባል አይችልም፡፡ ፍርድ ቤት ያሳለፈውን ውሳኔ ፖሊስ የማስፈፀም ግዴታ አለበት፡፡ አንዳንድ የተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ከወንጀል የራቁ እንዲሆን ህልውናቸው እንደሚያከትም መስሎ ስለሚሰማቸው ከወንጀል ጋር የውጥኝ ያሉ ይመስላሉ፡፡ ሰሞኑን መርህ ይከበር በሚል የተመሰረተው የአንድነት ቅጥያ ፓርቲ የእነ ፕሮፌሰር መስፍን ፓርቲ ወይዘሪት ብርቱካን ሚደቅሳን የፓርቲው ተቀዳሚ ሊቀመንበር አድርጎ መርጧታል፡፡ የህግ ታራሚን የፓርቲ መሪ ማድረግ “ይቺ ጠጋ ጠጋ ...” ያስብላል።

ማረሚያ ቤት ያለችን ግለሰብ በህግ አግባብ እንቀሳቀሳለሁ የሚል ድርጅት ሊቀመንበር አድርጎ መምረጥ ምን ዓይነት አካሄድ ይሆን? ይህን ያልኩበት ምክንያት የእነ ፕሮፌሰር መስፍን አዲስ የማፍያ ቅጥያ ድርጅታቸው ይህግ ታራሚዋን የፖለቲካ ፓርቲ አመራር አድርጎ መምረጥ በራሱ ከወንጀል ጋር መሳሳብ ይመስለኛል፡፡ ሌላው የ1997ቱ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሳዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ህግ አንድ የህግ እስረኛ በአንቀጽ 123-125 በተገለፀው መሰረት የሲቪሊና የፖለቲካ መብቶች እንደሚነጠቁ ይገልጻል ፡፡ እንዲህ ያለው ቅጥ ያጣ አካሄድ ህጋዊ መንገድን የሚከተል ፓርቲ አሰራር አይመስለኝም። የሙጥኝ ያለ

ፓርቲ ሲከራርምማ የወንጀል መቀፍቀፊያ ይመስለኛል፡፡ እነ ፕሮፌሰር በተማማተ የሂሳብ ስሌት የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት ይመስለኛል በማረሚያ ቤት የምትገኝን የህግ ታራሚ የፓርቲ አመራር አድርገው የመረጡት፡፡

በህግ አግባብ የተቋጨ ጉዳይ የምርጫ አጀንዳ ለማድረግ የሚሞክሩ ፓርቲዎችና ግለሰቦች የወንጀል ህግ አንቀጽ 480 ሥር የተደነገገውን የወንጀል አድራጊውን ያሞገሰ ወይም አበጅቷል ያለ እንደሆነ ወይም ዓለማውን ከተቀጣው ሰው ጋር አንድ በማድረግ የጥፋተኛውን ድርጊት መደገፍ በእሥስራት እንደሚያስቀጣ ስለሚያስረዳ ህብረተሰቡ ለራሱ ሠላም ዘብ በመቆም ከመንግስት ጋር በመሆን ህግ የሚጥሱትን እየተከታተለ ማጋለጥ አለበት እያልኩኝ ፤ ይህንን አጀንዳ የሚያራግቡ ፓርቲዎችና ግለሰቦችም እንደሞኝ የሞተ ጉዳይን ፈልጎ አጀንዳ በማድረግ ወደ ስልጣን ማሻቀብ ጊዜ ያለፈበት ፋሽን በመሆኑ ቢቀር ይመረጣል እላለሁኝ ፡፡